# Remind፣ ParentSquare፣ ParentVUE—

# ልዩነታቸው ምንድን ነው?

**አንዳንድ ነገሮችን እናጥራ።**

**ቤተሰቦች አንዳንድ ጊዜ "Remind"፣ "ParentSquare"፣ እና "ParentVUE" የሚባሉትን ሲመለከቱ እንደሚገርማቸው እናውቃለን—እነዚህ ሁሉ አንድ አይነት አይደሉም እንዴ? በአጭሩ መልሱ: አንድ አይደሉም ነው።**

እያንዳንዳቸው የሚያገለግሉት ለተለያየ ዓላማ ነው። እያንዳንዱ መድረክ ምን እንደሚሰራ፣ ከልጅዎ ትምህርት ቤት ጋር እንዴት እንደሚያገናኝዎት፣ እና በጣም የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት ወዴት መሄድ እንዳለብዎት ለመርዳት የሚያግዙ ጥቂት ጥያቄዎችን እና፣ አስፈላጊ መልሶችን እዚህ ያገኛሉ።

## "Remind" እና "ParentSquare" ምንድናቸው?

"Remind" እና "ParentSquare" MCPS ት/ቤቶች፣ መምህራን፣ተማሪዎች፣እና ወላጆች መካከል ለግንኙነት የሚያገለግሉ የመልእክት ማስተላለፊያ መድረኮች ናቸው።

## ሁለት የመገናኛ መድረኮች ያስፈለጉት ለምንድነው?

"ParentSquare" ላይ—"Remind" ይገኛል። ትምህርት ቤቶች ከጃንዋሪ 2026 ጀምሮ ከ "Remind" ወደ "ParentSquare" ይሸጋገራሉ።

## ለልጄ ትምህርት ቤት "Remind" ወይም "ParentSquare" እንዴት መመዝገብ እችላለሁ?

ትምህርት ቤትዎ "Remind" ወይም "ParentSquare" እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ መግለጫ ይሰጥዎታል።

## "ParentVUE" እና "MyMCPS Classroom" ምንድነው?

"ParentVUE" ትምህርት ቤቶች ስለ ተማሪ ውጤት፣ የትምህርት ክትትል፣ መርሃ ግብር፣"MyMCPS Classroom" መክፈቻ፣ እና ሌሎችንም ጉዳዮች በዋናነት ከቤት -ወደ- ትምህርት ቤት መረጃ የሚያስተላልፍ የወላጅ ፖርታል ነው። "ParentVUE" ድረገጽ ላይ ወይም ሞባይል መተግበሪያ ላይ ተደራሽ ነው።

## "MyMCPS Classroom (Canvas)" ምንድን ነው?

ይህኛው መምህራን ለኮርስ ማኔጅመንት፣ ለውጤት አሰጣጥ፣ ለግብረመልስ፣ ለቤት ስራዎች፣ እና ለቅንጅት ሥራ የሚጠቀሙበት የማስተማሪያ ማኔጅመንት ስርዓት ወይም ዲጂታል የትምህርት መድረክ ነው። ወላጆች የማስተማሪያ መረጃ እና ግብዓቶችን ለመመልከት “observer” አካውንት መጠቀም ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ እዚህ ጠቅ ያድርጉ።

## የልጄን መርሃ ግብር የማገኘው የት ነው?

"ParentVUE" ይክፈቱ የልጅዎን ስም ይምረጡ። "CURRENT SCHEDULE"/ ጠቅ ያድርጉ።

## የልጄን መርሃ ግብር ካላገኘሁ ምን ማድረግ አለብኝ?

ለልጅዎ ትምህርት ቤት ይደውሉ። "ParentVUE" በየጊዜው የሚዘምን ነው

**ለተጨማሪ መረጃ፣** MCPS የቴክኖሎጂ መረጃ እና የወላጆች ድጋፍ **ይመልከቱ።**